# አውራምባና አዲሳባ፤ የወቅቱ ሁኔታ

**በምትኩ አዲሱ** የሚሌኒየም እንቁጣጣሽ በሚል ርዕስ ከተጻፈው የቀጠለ።

**መግቢያ**

ሚዛን ማጣት ተንሠራፍቷል። እውነት ወገናዊ ሆኗል። እልህ አይሎ ፍትኅ ተዛብቷል።

የፈረንጆች አዲስ ዓመት ብዙ ወሬ አሰማን፣ ብዙ ጉድ አሳየን። ከእስር የተፈቱት የአገር መሪዎች በየፊናቸው፣ እንደ አስተናባሪዎቻቸው ብዛትና ብርታት ንግግርና ማብራሪያ ሲያሰሙን ሰነበትን። ብዙ ተንጫጭተን እንደቆየን ሰዬ አብርሃ መጡ ተባልን። ጥቂት ድረ ገጾች ይህንኑ በቃላትና በቀለማት ያዳንቁ ጀመር።

ስለ ሰዬ ጥርና የካቲት ላይ የታየው የጽሑፍ ካፍያ ለጊዜው ያባራ ይመስላል።[1] ብሶት ያለበት ብሶቱን አሰምቷል፤ አንደኛው፦ “ሰዬ አሰብን ያሰመልሱልናል?” “ኢትዮጵያና ኤርትራ ለምን ተለያዩ?” ሲል፣ ሌላኛው ተቀብሎ፦ “ተስፋችን ናቸውና… አትንጫጩ…” ሲለን ከረምን። [0.1]

ሁኔታው ሊሠጥም የሚወራጭን ሰው አኳኋን አስታውሶናል። የሚታደገንን ሰው በምኞታችን ልክ ልናበጅ እንሯሯጥና ወዲያው ተገልብጠን ረብሻ ስንፈጥር ታይተናል። እንደ እውነቱ ከሆነ በእምነትና በይቅርታ መንፈስ ካልሆነ በስተቀር ምንጊዜም እርስ በርስ መቀባበል አንችልም። ሰው ሆኖ መሣት ያለ ነው፣ ከስሕተት መማርም ያለ ነው፤ ሲጸጸት ይቅር ማለትና ዳግመኛ እድል መስጠት ደግሞ ፈጣሪም የሚወደው ነው። ሆኖም ይህን ቸርነት ለሌሎች ለማዳረስ እስካሁን ፈቃደኛነት አለመታየቱ ገርሞናል። ሊያረጋጉንና ሊያያይዙን የሚችሉት እንግዲህ እውን ሰዬ ይሆኑ?

**ወገናዊ እውነት**

አጥጋቢ ማብራርያ ያልተሰጣቸው ጥያቄዎች ዛሬም ቀርተዋል። በመጀመሪያ፣ ክቡር ሰዬ እንዴትና በየት በኩል አልፈው ነው ከርሸሌ ካወረዷቸው ጓዶቻቸው እጅ የተዋረደውን ብሔራዊ ኅልውና መታደግ የሚችሉት? ወይም በዋነኛነት የተሳተፉበትን ብሔራዊ በደል የሚያቃኑት?[2] ደግሞስ ከማን ጋር ሆነው ነው በልባችን የጫሩትን ተስፋ[3] እውን የሚያደርጉት? [አንድ መሪ በዙሪያው በሚሰበስባቸው ሰዎች ዓይነት ይመዘናልና።]

ወቅቱ ጥያቄ የምንጠይቅበትና አብረን መልስ የምንሻበት ወቅት ነው። መተማመንና መረጋጋትን ለመፍጠር ይኸ አስፈላጊ ነውና። እኛም ምናልባት ቢቀናን ድብቅና ልዝብ ፖለቲከኞቻችንን በቃል ብዛት ኮርኩረን ፍንጭ ለማግኘት እንታገላለን።

የነክቡር ገብሩ አሥራት “ዓረና ትግራይ” በፓርቲነት መመዝገብ፣ የክቡር ሰዬ መፈታትና የአንጋሹም ክፍል ሆነ የተቀሩት ከገኘው ክፍል ጎራ መውጣት ምን ያስታዝበናል? እንደ አዲስ፦ “አሰብን በሕግ እናስመልሳለን፣” “አንድነትና ኢትዮጵያዊነት” ወይም “ኢትዮጵያና ኤርትራን ማስማማት ይቻላል” የሚለው ዘይቤ አሁን መሰማቱ ምን ይጠቁመናል? የማናውቀው የተቀናበረና የተመከረ ጉዳይ ይኖር ይሆን?

---

[1] በተኮላሃጎስ ዶት ኮምና በኢትዮሚድያ ዶት ኮም ላይ ብቻ ወደ አስራ አራት የሚደርሱ ጽሑፎች በተጠቀሱት ወራት በእንግሊዝኛ ተለጥፈው ተነብበዋል።
[2] አንደኛው በደል ምሥጢረኛነት ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልተነገረው ውንዥብር ላይ የሚገኝበት ብዙ ጉዳይ አለ።
[3] “የኢትዮጵያ ሕዝብ ተስፋ መቁረጥ የለበትም” “እስር ቤቱ ኦሮምኛ ይናገራል” …

በውክልናው አገር አቀፍ የሆነ የጦር ሠራዊት ለማደራጀት ምን እርምጃ ይወሰድ? የሰዬ ጥረት ከኤርትራ ጋር ለሚኖረው ጦርነት እንደ ቀድሞ አልታለል ያለውን ሕዝብ ልብ ለማለዘብ ታስቦ ይሆን?[4]

ሰሞኑን የሚታየው አሠላለፍ የተያዘው አሠራር እንደማያዘልቅ ከመገንዘብ የተነሣ ያለውን ለማጽናትና ዕድሜ ለማራዘም እንደሆነስ?[5] የምንሰማው ምን ያህል አስተማማኝ ነው? የውጭ መንግሥት እጅ ይኖርበት ይሆን? እስካሁን ካየነው የተለየ ምን መሠረታዊ ለውጥ ይመጣልናል ብለን እንጠብቃለን? [ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሥልጣን እለቅቃለሁ ከማለታቸው ጋር እንዴት ሊያያዝ ይችላል? ከቅንጅት መሪዎች መካከል ከየትኞቹ ጋር ምን ዓይነት ስምምነት ላይ ተደርሷል? መሠረታዊ ችግራችንስ ንኡሳን ብዙሃኑን ሊወክሉ አይገባም የሚል አልነበረም ወይ?] ደግሞስ ሰዬ እድሉ ከተሰጣቸው በኋላ እንደታሰበው ሆነው ባይገኙ በፈቃዳቸው ሥልጣን ይለቅቃሉ? ሥልጣን ለማስለቀቅ እኛስ ምን አማራጭ ይኖረናል? ወይስ አያገባንም? ወይስ ሌላ ጊዜ እናስብበት?!

**የሚሌኒየሙ ትዝታ**

ሚዛን ማጣት ተንሠራፍቷል። ባለፈው መስከረም ወር ያከበርነውን ሚሌኒየም እስቲ ዳግም እንቃኝ። በክብረ በዓሉ ላይ ከፍተኛ ሥፍራ የተሰጣቸው ግለሰብ ቢኖሩ ክቡር ሼኽ አላሙዲ ናቸው።[6] እንደ እውነቱ ከሆነ ካሳዩት ታታሪነትና በጎ ሥራ አንጻር እጅጉን ሊመሰገኑ ይገባል። ዳሩ ግን የርሳቸው ጥረት እክል ቢገጥመው ብሎ ማሰብ በአገሪቱ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ማኅበራዊና ኢኰኖሚያዊ ቀውስ ለማርገብ ያስችላል፤ ይህ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። ኋላ የምንመለስበት ነጥብ ይህንን እውነት የሚቀናቀን ሳይሆን የወቅቱን ሁኔታ ለማስረዳት እንደ ሆነ አንባቢው ካሁኑ ያስተውል።

የሚሌኒየሙ ክብረ በዓል በሌሎች ከተሞች የተካሄደ ቢሆንም ቁንጮ ሆና የከረመችው ያቺው አዲሳባ ናት። ስለ ግለሰቡና ስለ መዲናዋ ገናናነት እንከን የሌለ እስኪመስልና ጥያቄ ማንሳት እስከሚያስወግዝ ድረስ በድረ ገፅ ተለጥፎ ተነብቧል። ሆኖም ማንም ከተጠያቂነት በላይ ሊሆን አይችልም፤ አይ-ገ-ባም። የአገር ፍቅር ለጥቂቶች የተሰጠ ነፃነት አይደለም፤ ወይም የሌሎችን ፈቃድ ያለ ጥያቄ ማስተጋባት አይደለም፤ ለአንዳንዶቻችን ባይስማማንም ለጋራ ጥቅም የራስን አሳብ ሳይቆጠቡ በግልጽ ማሰማት አማራጭ አይገኝለትም።

**ከፊልና ሙሉ ገጽታ**

አንድን ሁኔታ እንደሚገባ ለመረዳት ቢያንስ ከሁለት አቅጣጫ ማየት ያሻል። በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ የኢትዮጵያ ሁኔታ በገጠሬው፣ በከተሜውና በሰደተኛው ዓይን ሲገመገም የተለያየ ግንዛቤ ማስከተሉ አይቀርም። ስለሆነም፣ የሴት ዜጎች አመለካከትና የወንድ ዜጎች አመለካከት የተለያየ ይሆናል። የአዛውንቱና የወጣቱም። የደሃውና የባለጸጋውም። የቆለኛና የደገኛም፤ አገር ውስጥ የቀረውና ከአገር ውጭ የፈሰሰውም፣ ወዘተ። ነገርን ከአንድ ወገን ብቻ ማየት ጉዳት ያስከትላል። እውነቱን ያዛንፋል። ጨፍ ይዞ ወደ ማውራት፣ ከፊሉን የተሟላ ነው ወደ ማለት ያመራል።

✧✧

---

[4] "ጦርነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ምርጫ አይደለም" ኅዳር 17/1999። ቅንጅትኢትዮጵያ ዶት ኦርግ።

[5] ጠ/ሚ መለስ፦ የሶማሌ ዘመቻ በሁለት ሳምንት ውስጥ ይጠናቀቃል እንዳላሉ ሁሉ "የማንወጣበት ማጥ" ሆኖብናል ያሉትንና "በኦርቶዶክስ ኢትዮጵያ" ላይ ከካታርና ሌሎች ዓረብ አገሮች ጥቃት እየተፈጸመብን ነው ያሉትን ለምሳሌ ያህል መጥቀስ ይቻላል። (ቢ.ቢ.ሲ. ራዲዮ፣ ኖቬምበር 27/2007። ጋርዲያን ኮ ዩኬ ድረ ገጽ፣ ጃንዋሪ 25/2008።)

[6] ሼኹ በአባት የመናዊ እንደ ሆኑና ከ43 ዓመት በፊት በ1965 (እንደ አውሮጳ አቆጣጠር) የሳውዲ ዜግነት እንደ መረጡ ተነግሮናል። የርሳቸውን ስም ያነሳነው ለውይይት ከርሳቸው ይልቅ የሚያመቸንን ስላላገኘን ብቻ ነው፤ ከሼኹ ጋር የሚተካከሉ አቶ ክብረት የሚባሉ ቱጃር ቢኖሩ ኖሮ አቶ ክብረት እንል ነበር ማለት ነው!

አምስት ዓይነ ስውራን ዝሆን “ለማየት” ዝኆኑ ወደሚጠበቅበት ሠፈር አመሩ ይባላል። መቸም በዳበሳ ነውና ጎብኝተው ሲጨርሱ ስላዩት ዝኆን እርስ በርስ መነጋገር ይጀምራሉ። የዝኆኑን ጐን የዳበሰው፦ ግድግዳ ይመስላል አለ። ጥርሱን የዳበሰው፦ ጦር ይመስላል አለ። ኩምቢውን የነካ፦ ዘንዶ ይመስላል አለ። እግሩንና ጉልበቱን የደባበሰ፦ ወርካ ይመስላል አለ። ጅራት የደረሰው፦ ሽረ ገመድ ይመስላል አለ።

ነገር ከአንድ ጐኑ ብቻ ሲታይ እንደዚህ ያስታል። አሳብ በመለዋወጥና ተከባብሮ በመቀባበል ውስጥ ግን የተሟላውን እውነት መገንዘብ ይቻላል ማለት ነው።

## ዋነኛ ጥያቄ

ዋነኛው ጥያቄ ሚዛናዊነትን ለመቀዳጀት ምን ማድረግ ይገባል የሚለው ነው። ሚዛን ለመጠበቅ በቅድሚያ ምድር ያንድ ሰው፣ ያንድ ጾታ፣ ያንድ ጎሳ፣ ያንድ ፓርቲ፣ ያንድ ክልል፣ ያንድ ቀለም፣ ያንድ ሃይማኖት ወይም ያንድ ትውልድ ብቻ እንዳልሆነች መረዳት ያሻል። የአገርን ሉዓላዊ ክብር ሳያስጠብቅ የግል መብትን ማስከበር እንደማይቻል ማስታወስ ይ-ገ-ባል። ሚዛን ለመጠበቅ በሥፍራና በጊዜ ውስን እንደሆኑ ማወቅና ከግለኛና ከጎሰኛ አመለካከት ይልቅ የጋርዮሹ እንደሚያዘልቅ መገንዘብ ያስፈልጋል። ጥበብ ራሷን የምትገልጠው ለትሑታን እንደሆነ ማወቅ ከብዙ ድካም ያድናል። ኩሩዎችና ብልጦች ግን የራሳቸውን ውሸት ከማመን ወዲያ አማራጭ አይኖራቸውም።

## ራስህን እወቅ፣ አዙረህ እይ

ከእግዚአብሔር በስተቀር የተሟላ አመለካከት ያለው የለም። ከአንድ ወገን ብቻ አይቶ የተሟላ ነው ለማስኘት መሞከር ግን የሰው ሁሉ ደካማ ጎን ነው። በራሳቸው አሳብና ምኞት ለተዋጡ ይኸ ወጥመዳቸው ነው። ለምሳሌ፦

- አጼ ምኒሊክ መንግሥታቸውን ያጸኑት በነፍጠኛውና በአካባቢው አድር ባይ ብርታት እንደሆነ ሲነገር እንሰማለን። አሁን ያለው መንግሥትም ያንኑ እየደገመው እንደሆነ ግን ማመን ሆነ ማሰብ አቅቶታል። ይባስ ብሎ ኦሮምፋ የሚናገሩ የትግራይ ተወላጆችን በኦሮሚያ ክልል በማሠማራት ላይ ይገኛል። [1] ያው እንደ ምኒሊክና እንደ አጼ ኃይለ ሥላሴ “ባገሩ በሬ” ማረሱን ተያይዞታል። ሁሉም ተራ ሲደርሰው በራሱ ላይ ዓይነ ስውር ነው፤ በሌላው ላይ ሲያነበንብ የኖረውን በተለያየ መልኩ ይደግመዋል ማለት ነው!

- ይኸው መንግሥት አንድን ሕዝብ በጦር ኃይል ብዛት መግዛት እንደማይቻል ከደርግ ጋር ባደረገው ፍልሚያ አረጋግጧል፤ እራሱ ግን ያንኑ እያደረገው ነው።

- አይደፈሩም የተባሉት የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥትና ደርግ ወድቀዋል። የወደቁትም የሕዝቡን ጥያቄ ለማፈን በመሞከራቸው ብቻ ሳይሆን የኃያላን መንግሥታት ድጋፍ እንደማያስተማምን ካለማጤንም ጭምር ነበር። ሁለቱንም መሪዎች በመጣል ረገድ የዚህ መንግሥት አባላት ተሳታፊ ቢሆኑም እነዚሁ ግን ሥልጣን በያዙ ማግስት ያን ሁሉ እውነት ዘንግተውታል።

- አንዳንዶቻችን ጎሰኛነትን ለማጽናት ዛሬ እውነት ነው ብለን የምንጽፈው ነገ በታሪክ እንደሚያስወቅሰን ማስተዋል ተስኖናል። በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን፣ ቀጥሎም በደርግና በኢሕአዴግ ዘመን ምድር አልበቃቸው ያሉ ሁሉ አንዳቸውም ከሌላው ሳይማሩ ዛሬም ስንፍናቸውን ሲደግሙት እያየን ነው። በምሑርነት ተገን ለጎሳቸው ሽንጣቸውን ገትረው መቆማቸው ለእውነትና ለፍትሕ ከመቆም


አፈናቅሎአቸዋል። እነዚህም ከትጥቅ ትግል ይልቅ[7] የሰላማዊ ትግልን ፍቱህነት ሲያስረዱ ስለ ሰላም ገድዷቸው ሳይሆን ያለው እንደ ነበረ እንዲቀጥል በማሰብ ነው። ሌሎችም ልኩን እያወቁ ዝምታን መርጠዋል፤ ዝምታቸው ግን ድጋፋቸው ለማን እንደሆነ እንደሚለፍፍባቸው ማን ባስታወሳቸው!


- ስለ አሳብ ነጻነትና የመናገር መብት የሚለፍፉ ነጻነቱን በማፈን ቀዳሚዎች ሲሆኑ ታይተዋል። ፕሮፌሰር መስፍን በአሜሪካን ድምፅ ራዲዮ ላይ ስለ ቅንጅት አመራር ቃለ መጠይቅ ሊሰጡ ነው የተባለ ዕለት ብዙ ጉጉት ታይቶ ነበር። ፕሮፌሰሩ ግን ለማንም የማይበገሩ ነፃ አሳቢ እንደ መሆናቸው ብዙዎች ሊሰሙ ያልፈለጉትን እውነት ሲናገሩ ተደምጠዋል። ከዚህ የተነሣ እንደ አምላክ ሲያገንኗቸው ከነበሩ ክፍሎች ሳይቀር ብዙ ችኩልና አሳፋሪ የቃላት ውርጅብኝ ደርሶባቸዋል። ሚዛን ማጣት። [1.1]



**አውራምባና አዲሳባ**

የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ ደግሞ ከአውራምባና ካዲሳባ አንጻር መመርመር ይቻላል። እርግጥ አዲሳባና አውራምባ ብዙ ይራራቃሉ። በቆዳ ስፋት ይለያያሉ። አዲሳባ አውራ ከተማ ነች፤ በአዲሳባነት የተመሠረተችው ከአንድ መቶ ዓመት በፊት በእተጌ ጣይቱና በአጼ ምኒሊክ ሲሆን ዛሬ አራት ሚሊዮን ያህል ሰው ይኖርባታል ይባላል። አዲሳባ ኢትዮጵያ ነች፣ ኢትዮጵያም አዲሳባ ነች፤ ሁሉን ዓይነት ብሔርና ብሔረሰብ አቅፋ ይዛለች፤ ደግሞ የአገር ባሕልና የዘመናዊነት መፋለሚያ ነች።

አውራምባ በአንጻሩ አዲስ አምባ ነች። መታወቅ ከጀመረች ገና ሠላሳ ዓመት አልሞላትም። ካዲሳባ ሰሜን ምዕራብ 650 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ አራት መቶ ያህል ኗሪዎች የሚኖሩባት መንደር ነች።

በሁለቱም ሠፈር የሁለት ግለ ሰቦች ስም ገንኖ ይታወቃል። ባዲሳባ የሳውዲው ነጋዴ ሼኽ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ፣ ባውራምባ ደግሞ ገበሬው ዙምራ ኑሩ። የሁለቱም ዕድሜ ወደ ስድሳኛው ይጠጋል። አንደኛቸው ሶሻሊስት፤ ሌላው ካፒታሊስት ነው። ሼኹ የዛሬ 15 ዓመት ይኸ መንግሥት ጥሪ አድርጎላቸው እንደ መጡ ሰምተናል። [1.2] ዙምራ ኑሩ በበኩሉ ሁለት መንግሥት አሳልፎ ሦስተኛውን ጠምዷል።

ሁለቱም የዘመናዊን ትምህርት አስፈላጊነት የተገነዘቡ ይመስላል። የሼኹን መደበኛ የትምህርት ደረጃ ባናውቅም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት እንደተሰጣቸው ሰምተናል። ስለሆነም ሙሉ ማዕረጋቸው፥ ክቡር ሼኽ ዶክተር መሐመድ ሁሴን አላሙዲ ሲሆን፣ የዙምራ ባጭሩ፥ ጓድ ዙምራ ነው፤

[7] የአንዳንዶችን አቋም ለመግለጽ እንጂ የትጥቅ ትግልን ለመደገፍ አይደለም።

የትምህርት ደረጃው ደግሞ ከመሠረተ ትምህርት ያለፈ አይመስለንም። ለዙምራስ የክብር ዶክትሬት ከሃራማያ ዩኒቨርሲቲ ቢሰጠው ይበዛበት ይሆን?

ሼኩን ከኢትዮጵያ አልፎ ዓለም ያውቃቸዋል። ዙምራ ኑሩን ስንት ኢትዮጵያዊ ያውቀዋል?

ሕዝብን፣ ዘመናትንና ምጣኔ ሀብትን ያካተቱ ውስብስብ ጉዳዮችን መመርመር ቀላል ባይሆንም ቀሊል ገጽታዎቻቸውን ወክሎ ማነጻጸር በቂ ግንዛቤ እንደሚሰጥ በማኅበረ ሰብ ጥናት ሊቃውንት ዘንድ የተመሰከረና የታወቀ ነገር ነው። ሁለቱ ወኪል ግለሰቦችና የሚገኙበት አድራሻ እንግዲህ ስለ ኢትዮጵያ ወቅታዊ ገጽታ ምን ያስረዱናል?

**አዲሳባና አውራምባ**

እንደ ዶክተር አብዱልመጂድ ሁሴን አባባል ከሆነ ሼኩ "አዲሳባን ከማንም ሰው ይልቅ በዓለም ካርታ ላይ ያሠፈሩ ግለሰብ ናቸው።" ስለዚህም፣ ሼራተን ሆቴል አካባቢ ከሚገኙት መንገዶች መካከል አንደኛቸው በሼኩ ወላጅ እናት ስም እንደገና እንዲሰየም ዶክተሩ አሳብ አቅርበዋል። [2]

ደግሞ፣ ከችሮታቸውና ከንግድ ሥራቸው ስፋት የተነሣ ከአገሪቷ ጠ/ሚኒስትር እጅ "የመጀመሪያውን ልዩ የሚሌኒየም የወርቅ ሜዳልያ" እኝሁ ግለሰብ ተቀብለዋል። ዙምራ ኑሩ ቀበሌውን ከመነሻው የቀረቀረ፣ ያደራጀና ያለማ ቢሆንም በዚህ ወቅት አልታሰበም።

ሼኩ የግላቸውን ሠላሳ ሚሊዮን የእንግሊዝ ፓውንድ [3] አውጥተው አዲስ አዳራሽ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ አሠርተዋል፤ ሽልማታቸውም እዚያው ተሰጥቶአቸዋል። በዚሁ ወቅት እርሳቸው፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩና ሌሎችም ንግግር አድርገዋል። ሼኩ ባደረጉት አጭርና ግሩም ባለ አንድ ገጽ ንግግር ላይ "አገሬ" ወይም "አገር" የምትለዋን ቃል 18 ጊዜ ጠቅሰዋል። [4] ለኢትዮጵያ ያላቸውን ብሩህ ተስፋና ቁርጠኛ ምኞት አብስረዋል። ምናልባት የርሳቸውን ንግግር ጠ/ሚኒስትሩ ቢያነብቡት ይሻል ነበር ወይ? አሰኝቶናል።

"ክልሌና ጎሳዬ" እንጂ "አገሬና ወገኔ" አትበሉ ስንባል በከረምንበት ዘመን የሁላችንን የወደፊት ዕጣ አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ እንኳ እየታየ ሌላው ይጨነቅበት በሚል ስሜት ተውጠናል። አገር አቀፋዊ አስተሳሰብ መንምኖ ክልላዊ ጎልውና ይጸናል ማለት ግን ሞኝነት ነው።

**የችሮታ ነገር**

አንዳንድ ጸሐፊያን ሼኩ ከአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ይልቅ ላገራችን ልማት እንደጣሩ ሊያስረዱን ሞክረዋል። [4.1] የነዚሁ ብዙ ሙገሳ ነገ ለምን ያገር መሪነቱንም ጨምረው አይረከቡም ወደ ማለቱ ቢያመራ አያስደንቅም። ስለ ግለሰቡ ችሮታ የሚወራው እውነትነት ባያጣውም ያለብንን ኃላፊነትና ብሔራዊ ግዴታ እንዳንወጣ ሰበብ ሆኖናል።

ደግሞስ ለአገር ያለን ፍቅር የሚለካው ከትርፋችን በምንሰጠው ስጦታ መጠን ብቻ ነው ወይስ ከጉድለታችንም በምናሳየው ጥረት? ለኔብጤ ቁራሽ እንጀራ ያቀበሉ እናትና በየዕለት ችግሩ የሚደራረሰው የአገራችን ሕዝብ ቸርነቱ ያነሰ ነው ማለት ነው? አይመስለንም።

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የሼኩን ጥረት ሲያስረዱ "አገሪቷንና ሕዝቡን ከመውደዳቸው የተነሣ ትርፍ ማምጣቱን እንኳ ገና ሳያውቁ" ብዙ የልማት እንቅስቃሴ አካሂደዋል ብለዋል። [5] ትርፍ እንደሚያመጣ ሳያረጋግጡ ንግድ ሥራቸውን የሚያንቀሳቅሱ ከሆነማ ለኪሣራ እየሠሩ ነው ማለት ነዋ! ይልቅ የንግድ

እንቅስቃሴአቸው በኢትዮጵያ ክልል ብቻ እንዳልተወሰነና በገንዘብ የማይተመኑ ሥነ-ልቡናዊና ማኅበራዊ ትርፍም እንዳቀዳጃቸው ማስረዳት ተገቢ ይሆን ነበር እንላለን።

**እርምጃዬና የኢትዮጵያ ሕይወት**

ከላይ በተጠቀሰው ክብረ በዓል ላይ ሼኹ በራሳቸው ወጭ የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናትን፣ የውጭ ቆንስላ ተወካዮችንና ጥሪ የተደረገላቸውን እንግዶች ሁሉ ጋብዘዋል። ከግብዣው በኋላ የሕይወት ታሪካቸው ከተወለዱባት ወልዲያ ወሎ ጀምሮ በቪዲዮ ተቀርጾ በእድምተኛው ታይቷል። አሁንም እንኳ በመንግሥትና በደጋፊዎቹ ድረ-ገፅ ተለጥፎ እየታየ ነው። [6] ባጭሩ፣ በዘመን መለወጫው ክብረ በዓል ላይ ለግለሰቡ ዋነኛ ሥፍራ ተሰጥቶአቸው ነበር ማለት ይቻላል። [6.1]

ዙምራ ኑሩን ያስተዋለውም የለም። እርግጥ መንደሩን የክልል ፖለቲከኞች፣ የውጭ አምባሳደሮችና ጋዜጠኞች አልፎ አልፎ ጎብኝተዋል፤ አድንቀውለታልም። አብሮ መኖር ባገራችን ያልተለመደ ባይሆንም ገበሬው ዙምራ ደሃ ሀብታም፣ ክርስቲያን እስላም፣ ሽማኔ እናጢ ሳንል አብረን ተጋርተን ብንኖር ከድህነት ለመላቀቅ እንችላለን የሚል አሳብ ሲያመላልስ ሠላሳ ዓመት አሳልፏል። ከዚህም የተነሳ ተቃውሞ ደርሶበታል። የርሱንና የአጋሮቹን ርስት አስለቅቀው ለሌሎች ሰጥተውባቸዋል፤ ያም ሳይገታቸው በብዙ ትግል ከፊሉ ተመልሶላቸው ተስፋ ሳይቆርጡ ዛሬም ራእያቸውን እውን በማድረግ ላይ ይገኛሉ።[7]

ሼኽ አላሙዲ ዝነኛውን ሆቴል ሼራተንን ሲያሠሩ ባለመሬቶቹን በመንግሥት ትእዛዝ ማስነሳት ነበረባቸው። [7.1] እርግጥ ላስነሷቸው ኗሪዎች ኋላ ካሣ ከፍለዋል። ሆኖም ባለ መሬቶቹ በርስታቸው ላይ ለመቆየት ምርጫ እንዳልነበራቸው መረሳት የለበትም። አምላክ የጣለላቸውን ድንገተኛና ምርጥ የመሬት ይዞታ ሃብት አቆይተው ወይም ተደራድረው የናረ ትርፍ ለመቀበል አቅሙና የመንግሥት ድጋፍ እንዳልነበራቸው ማስታወስ ይበጃል።

ሼኹ ለብዙዎች የሥራ እድል እንደ ከፈቱ ግልጽ ነው። ዙምራም እንዲሁ። ልዩነቱ ያውራምባ ኗሪዎች እኩል ተወያይተው ካስፈለገም ዙምራን ሳይቀር ወቅሰው ኑሮአቸውን በመግፋት ላይ ይገኛሉ። በሥራቸው ትጉና ግልጽ ከመሆናቸው የተነሳ የአካባቢው ሕዝብ እምነት ጥሎባቸዋል። በአንጻሩ የሼኹ የንግድ እንቅስቃሴ ግልጽነት እንደሚጎድለውና ይህንኑ መተቸት ችግር እንደ ፈጠረባቸው አንዳንዶች ይናገራሉ። [8] ይህን ስንል ፈጥረው ስም ለማጥፋት የሚነሱትን ማለታችን አይደለም።

ሌሎችም ሼኹ ከመንግሥት ጋር ያላቸውን ቅርበትና የውጭ ዜጋ ሆነው ሳለ በአገራችን ፖለቲካና የገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ ያላቸውን ከፍተኛና ብቸኛ ሚና በማስመልከት ጥያቄ አንስተዋል። [9] እርግጥ ካለው መንግሥት ጋር ሳይስማሙ ሥራቸውን ያንቀሳቅሱ ማለት የማይመስል ነው። ሆኖም ካልተደላደለና በፖለቲካና በንግድ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ስልቱ ሕጋዊነትና ግልጽነት ከጎደለው መንግሥት ጋር የጠለቀ ቅርርብ መፍጠር ግንኙነቱ ሁሌ ሕጋዊነትና ግልጽነት ይኖረዋል ማለት አስቸጋሪ ነው።

ዙምራ ገበሬው በተጨማሪ ሥራን ለሴትና ለወንድ ብሎ በፆታ መለየት ተገቢ አይደለም በማለት እያንዳንዱ ሥራ የማይንቅበትን ሁኔታና ባሕል ፈጥሯል። ከዚህ የተነሳ ሴቶችም እንደ ወንዱ በቀበሌው እኩል ተሳትፎና ድምጽ አግኝተዋል። አውራምባን ሥራ አጥ ወጣት ከሚፈላባት ካዲሳባ ጋር ማነጻጸር ባገር ደረጃ ከፍተኛ ግምት እንድንሰጣት ያስገድደናል ብንል ከእውነት የራቅን አንሆንም።

በአዲሱ ዘመን መግቢያ ላይ የታየው ክብረ በዓልና የተሰማው ሙገሳ አውራምባና አዲሳባን አገሪቱ ከምትገኝበት ወቅታዊ ሁኔታ አኳያ እንደገና እንድንታዘባቸው ይገፋፋናል። መንግሥት መመሪያዬ ብሎ

ያስታወቀን "ከገጠር ወደ ከተማ ልማት" [9.1] ካዲሳባ እንዳላለፈና ቢበዛ ካዲሳባ መቀሌ እንደደረሰ ብዙዎች ሲተቹ ይደመጣል። [9.2]

## ምን እንበል?

ነጋዴው ሼኹና ገበሬው ሁለቱም የአገራችንን አኳኋን ሽቅብና ቁልቁል እንድናይ ይጋብዙናል። የጥቂቶችን እጅግ መበልጸግና የብዙሃንን የደቀቀ ኑሮ አጉልተው ያሳዩናል። ይህም ማለት ሁለቱም ወገን ወደ አንድ ይጠቃለል ማለት አይሁንብን፤ የማይመስል ነውና። ይልቅ እየባሰበት ያለውን የኑሮ ደረጃ መራራቅ እንዴት ማቀራረብ ይቻላል ልንልና በድርጊት ምላሽ ልንሰጥበት ይጠበቅብናል። የሼኹ ብልጽግናና የሚፈስሰው የውጭ እርዳታ ብዛት ሲታይ ኢትዮጵያ በልማት ገሰግሳለች ወደሚለው ወደ ተሳሳተ መደምደሚያ ይመራናል።

የውጭ እርዳታና ችሮታ ዕዳና ሱስ እንጂ መብት ስላልሆነ፣ ሲቋረጥ ብዙሃኑን ደሃ ከባሰ አደጋ ላይ እንደሚጥለው የተዘናጋን ይመስላል።

እርግጥ ሼኹ የግል ሀብታቸውን በመሰላቸው ጉዳይ ላይ እንዳያውሉ የሚከለክላቸው የለም። በጎ ሥራቸው ግን የሕዝብ ልብ በተቀበላቸው አርቲስቶች፣ ምሁራን፣ ስፖርተኞችና ባለሥልጣናት ላይ አጥብቆ ሲያተኩር ጥያቄ ይፈጥራል። በጐ ሥራ በስውር ቢደረግስ አይሆንም ወይ ያሰኛል።

አውራምባና ዙምራ ኑሩ በዚህ ወቅት አለመታሰባቸው የመንግሥት አቋም የተንጋደደ ለመሆኑ ጉልህ ማስረጃ ነው። በሌላ አነጋገር፣ ተጠንቅቀን ከምንናገረው ይልቅ ሳይታሰብ የምናወጣው ቃል እውነተኛ አቋማችንን ይገልጥብናል።

ለማንኛውም፣ በአዲሳባ ከተማ ዋነኛ የሆነን መንገድ "አውራምባ ጐዳና" ብሎ መሰየም ተገቢ ብቻ ሳይሆን ለብዙሃኑ ሕዝብ ሞራል ግንባታ አስፈላጊ ነው። በተጨማሪ፣ ለገበሬው ዙምራ ኑሩና መሰሎቹ ሌላ "የመጀመሪያው ልዩ የሚሌኒየም የወርቅ ሜዳልያ ሽልማት" ተዘጋጅቶ በአገሪቱ ፓርላማ ፊት ይሰጣቸው እንላለን።

የኢትዮጵያን ዐበይት ፈተናዎች ማለትም ድህነትና የጎሳ ፖለቲካን ለመቋቋም መንገዱ በአውራምባ በኩል ይለፍ ወይስ ባዲሳባ ለምትለዋ ጥያቄ መልስ መሻት ይኖርብናል። ሁለቱን መነጣጠል አስፈላጊ ባይሆንም ድህነት በችሮታ ብዛት ዘላቂ መፍትሔ እንደማያገኝ፣ ግላዊ ችሮታም ቸርነትና ትጋትን ሳይሆን ተመጽዋችነትን እንደሚያጠናክር ግልጽ እየሆነ መጥቷል። ባጭሩ፣ በጎ አድራጎት ከባዶ ይሻላል ማለት እንጂ ዘላቂ መፍትሔ አይሆንም።

ችሮታ የግለሰቦች ፈቃድ እንጂ የዜግነት መብት አይደለም። ስለዚህም ዜጎች በየክልላቸውና ከክልላቸው ውጭ ተቻችለውና ተረጋግተው ራሳቸውን የሚያስተዳድሩበትን ሁኔታ መፍጠር የመንግሥት ተቀዳሚ እቅድ መሆን ይኖርበታል። ጎሳና ጎሰኛነት ደግሞ በራሳቸው በጎ ወይም ክፉ ባይባሉም ለፖለቲካ ማራመጃ ሲውሉ ማኅበራዊና ብሔራዊ አመለካከትን እንደሚሸረሽሩ በነዚህ ዓመታት ግልጽ የሆነልን ይመስላል።

## ሚዛን መጠበቅ

ሚዛን ማጣት የኢትዮጵያን ፖለቲካ አክራሪ ገጽታ አጉልቶታል። ማኅበራዊ ኃይላት አሠላለፋቸው ዘወትር ጥግ እንጂ መሃሉንና መገናኛውን አይገነዘቡም። በሌላ አነጋገር፣ ጠርዙን ግንጥልነት እምብርቱን ወናነት ያዘወትረዋል ማለት ነው። በዚህም መሠረት ደሃ ወይም የናጠጠ ከበርቴ ነው። መሃይም ወይም ባሕሉን

የጣለ ሊቅ ነው። ረሐብተኛ ወይም ጠግቦ የሚያድር ነው። እስረኛ ወይም የአገር መሪ ነው። መግዛት ካልቻለ አይ-ገ-ዛም። ወዳጅ ወይም ጠላት ነው። የሚፈለገውን ካልለፈፈ ጠላት ነው፣ በአመለካከት ከተስማማ ብቻ ወዳጅ ነው። ይህን በሽታ ቀርፎ ለማስወገድ እንግዲህ ቢያንስ አንድ ትውልድ ማለፍ የሚኖርበት ይመስለናል።

- አብዮት፦ "ሃይማኖት አደንዛዥ ዕፅ ነው" አለን። ከሃይማኖተኛነት ሊያላቅቀን ቆረጠ። እንኳንስ ሊያላቅቅ አባባሰው። ዙምራ ኑሩ ደግሞ ክርስቲያን እስላም ማለት ለምን ያስፈልጋል እያለን ነው። እንዲያውም ሃይማኖት አያስፈልግም ወደ ማለቱ ተቃርቧል። ሩስያዎች፣ ቻይናዎችና ደርግ በድምሩ ለ150 ዓመታት በሃይማኖት ላይ ዘመቻ አካሂደው ያቃታቸውን ተራውን እየሞከረው ይገኛል።

  የሰው ታሪክ ጅማሬ፣ ግሥጋሴና ፍጻሜ ከሃይማኖት እንደማይጠራ ዙምራና አዳናቂዎቹ ምዕራባውያን የዘነጉት ይመስላል። እርግጥ፣ "ክርስቲያን እስላም ማለት ምን ያስፈልጋል?" የሚለው አሳብ "እንቻቻል" ከሚል በጎ ከሚመስል አሳብ የመነጨ ሊሆን ይችላል። ይህም የጠብና የጦርነት ምንጩ ሃይማኖት ነው ከሚል መሠረተ-ቢስ አመለካከት የመጣ ነው። አንዱን ችግር ለመፍታት ሌላ የባሰ ችግር መፍጠር ያሻል?

- "ሃይማኖት የግል ነው" እንላለን፤ ዘር ብለን በኔ እምነት ቀለበት ውስጥ ካልገባህ እስከ እነአንካቴው አላውቅህም፣ አልቀበልህም እንላለን። የራሳችንን እምነት እንደሚገባ ሳናውቅ ሌላው እንዲያውቅልን እንሻለን፤ የሌላውን እምነት አንጋድደን ማየት እንጀምራለን።

- "አገር የጋራ ነው" እንላለን፤ ወዲያው ደግሞ አሳብህ ከኔው ጋር ስላልተስማማ ዜግነትህ ያጠራጥራል ወደ ማለት እንሸጋገራለን።

- "ኢትዮጵያዊ ሥነ-ምግባር ...እና የአገር ፍቅር መንፈስ እንዲኖር" እንጥራለን እንላለን። ኢትዮጵያዊ ሥነ-ምግባርን የማይገነባ ተግባርና ባሕል ስናራምድ እንታያለን።

***መደምደሚያ***

ክቡር ዶክተር አብዱልመጂድ ከላይ በጠቀስነው ጽሑፋቸው ላይ እንደጠቆሙን ያንድን አገር የኤኮኖሚ እንቅስቃሴ መንግሥት ጠቅልሎ መያዙ ጠቃሚ አይሆንም። በአባባላቸው ላይ ብናክል፦ መንግሥት ዓላማውን በተዘዋዋሪ በሚፈጽሙለት በጥቂቶች እጅ ማድረጉም ተገቢ አይደለም። ሁለቱም የአገሪቱን የረጂም ጊዜ ኤኰኖሚያዊ ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ናቸውና። ውጭ አገርና አገር ውስጥ ለሚኖሩ ዜጐች አሁን የተጀመረውን የመቋቋም መምሪያ በበለጠ ማመቻቸት አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው።

ሼኹ ሰው እንደ መሆናቸው ቢሞቱ ወይም እንቅስቃሴአቸውን የሚያደላድል ሌላ መንግሥት ቢነሳ ወይም የዓለም ኤኰኖሚ ቢቃወስ ወይም የንግድ እንቅስቃሴአቸውን አቅጣጫና መጠን ቢለውጡ ብሎ ማሰብ አማራጭ የሌለው ብሔራዊ ግዴታ ነው። የዓለም ባንክ በየአገሩ እንደለመደበት ጣልቃ ገብቶ የኢትዮጵያን መንግሥት በዕዳ ሊይዝ መተማመኛ ሰጥቶ ይሆን? በኢኰኖሚና በንግድ ሙያ የሠለጠኑ ምሑራን በዚህ ረገድ ምነው ድምፅ አላሰማ አሉ? የመንግሥት መመሪያዎችና ስምምነቶች የአገራችንን የረጅም ጊዜ ጥቅም ምን ያህል ለአደጋ አጋልጠዋል? ብሔራዊ ፖሊሲ የሚታቀደው እኮ "ቀውሶች ቢከሰቱ ምን መዝለቂያ ተዘጋጅቷል?" ከሚለው ፅንሰ አሳብ በመነሳት እንጂ የነገሮች ፍጻሜና አካሄድ እንደ ተረጋገጠ በመቁጠር አይደለም። በሌላ አነጋገር፣ በአንድ ብርቱ ላይ መደገፍና አንድ አማራጭ ብቻ መያዝ አስተማማኝነት የለውም፤ እንዲያውም ቂልነት ነው።

Copyright © by Mitiku Adisu
March 10, 2008. All rights reserved

## ማስረጃዎች

]0.1] ኢትዮሚድያ። ተኮላሃጎስ ዶት ኮም። አይጋ ፎረም። አዲስ ቮይስ። ደቺአሉላ።
[1] ጂማ ታይምስ፤ "ሞር ትግራያንስ ዩዚንግ ኦሮሞ ኔምስ" 10/19/2007
[1.1] ኢትዮ ዛጎል። ኢትዮሚድያ። ኦክቶበር 17/2007። በእንግሊዝኛ።
[1.2] ናዝሬት ዶት ኮም። ፌብርዌሪ 28/2006። በእንግሊዝኛ።
[2] አዲስ ትሪቢዩን ዶት ኮም። "ታንክ ዩ፣ ሼኽ አላሙዲ" በዶክተር አብዱል መጅድ ሁሴን 01/06/2000
[3] ታይምስ ኦን ላይን፤ ሴፕቴምበር 10/2007። (በእንግሊዝኛ)
[4] የሼኽ አላሙዲ ንግግር፤ ሪፖርተር ጋዜጣ። 9/2007
[4.1] ግለሰቡ ያደረጉት አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ጥቂቱን በእንግሊዝኛ ኢትዮስፖርትስ ዶት ኮም ላይ አጣቅሰው ይመልከቱ።
]5] የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት። "መለስ ሼኽ አላሙዲን ሸለሙ" ሴፕቴምበር 14/2007፤ በእንግሊዝኛ።
]6] ዓይጋ ፎረም ዶት ኮም፤ ኢትዮጵያፈርስት ዶት ኮም። "ኢትዮጵያ ኢተርናል ላቭ -- ሼኽ መሐመድ አላሙዲ" ባለ-10 ክፍል ቪዲዮ
[6.1] ኢትዮጵያ ፈርስት ዶት ኮም ለሼኹ በተጨማሪ "ፐርሰን ኦፍ ዘ ሚሌኒየም" የሚል የምስክር ወረቀት ሰጥቷቸዋል። ጥቅሄር ተፈራ በበኩሉ አፄ ኃይለ ሥላሴን "ማን ኦፍ ዘ ሚሌኒየም" ብሎ በፊልም ቀርፆ ሲያቀርብ፣ ኢትዮጵያን ሚሌኒየም ዶት ኮም ደግሞ አፄ ምኒሊክን ሰይሟል። እንደዚህ ከቀጠለ፣ ዓመቱ ሳይገባደድ ሹመቱ ሁላችንንም ሳይደርሰን አይቀርም!!
]7] ክርስቲያን ሳይንስ ሞኒተር፤ "ፍትሕ ለሰፈነበት ማሕበረሰብ የአንድ ግለሰብ ራእይ በኢትዮጵያ" በእንግሊዝኛ። ኦገስት 21/2007
[7.1]ሼራተን ኤክስፓንሽን ሙቭስ ኦቨር 12,500 ፒፐል። አዲስ ፎርቹን ዶት ኮም፤ ኢትዮጵያፈርስት ዶት ኮም።
]8] ሼኽ አላሙዲ፤ አበጋዝ በለጠ (ጁን 24/2005)። ]ሼኽ አላሙዲን በተመለከተ ለአበጋዝ በለጠ
የተሰጠ መልስ፤ በሃና ዮሐንስ (ጁን 26/2007)፤ ተኮላ ሐጎስ ዶት ኮም። በእንግሊዝኛ።
]9] አዲስ ዜና። "አላሙዲ ለኢሕአዴግ ሲቀሰቅሱ ዋሉ" ሚያዝያ 18/1997። ኢትዮዛጎል። አዲስ ፎርቹን። ኖቬምበር 2007 [ሕገ-ረቂቀ 2003 ን ለመቀልበስ የሚደረገውን ሙከራ በማስመልከት]። ኢትዮዛጎል ዶት ኮም ኖቬምበር 6፣ 2007 ቪኪ ሃድልስተን ሕገ-ረቂቅ 2003 ን በመቃወም ያደረጉትን ዘመቻ በማስመልከት ከሼኹ ጋር ያላቸውን ወዳጅነት ጠቅሷል። በእንግሊዝኛ። "ካንትሪ ኢኮኖሚክ ሪፖርት" ኖቬምበር 2004፤ ገጽ28፣ በ ጂ. ሃንሰን።
[9.1]ኮሜንትስ ኦን ዘ ፖለቲካል ክራይሲስ ኢን ኢትዮጵያ። ኢትዮሚድያ። ኖቨምበር 14/2005። ደረሰ ጌታቸው፤ ፔዘንት ሪፍሌክሽንስ...፤ ዌድ-ኢትዮጵያ ዶት ኦርግ። 2003። ደሳለኝ ራህመቶ፤ ቃለ ምልልስ፤ ኢሪን ዶት ኦርግ። ኦገስት 14/2003
[9.2]"ኦን ዘ አይደንቲቲ ኦፍ ፒ ኤም መለስ..." በንጉሴ አየለ። ኢትዮጵያንስ ዶት ኮም።

## ተጨማሪ ማስረጃዎች፦

- የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት (በእንግሊዝኛ)። ኦል አፍሪካ ዶት ኰም፣ ኦክቶበር 1/2007
- ናዝሬት ዶት ኰም፣ በእንግሊዝኛ፤ 4/2005
- አውራምባ። በኃይለሚካኤል ማሞ። ኢትዮሚድያ ዶት ኮም። 5/22/2006፤ በእንግሊዝኛ

- ጁሊ ዢራርድ። ፎቶ። 10/2007። ፎቶ። ዴቪድ ሺን። አይላቭኮብ ዶት ኮም።
- ዘ ሪፖርተር፤ ሴፕቴምበር 29/2007።